# የመጽሐፍ ግምገማ

## በይነዲሲፒሊናዊ ንባብ በ*አለመኖር* ረጅም ልቦለድ

አንተነህ አወቀ[1]፣ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## መግቢያ

በዚህ የመጽሐፍ ዳሰሳ ተተኳሪ የሆነው ልቦለድ ርዕስ *አለመኖር* ሲሆን ደራሲው ዳዊት ወንድምአገኝ (ዶ/ር) ነው፡፡ ዳዊት ወንድማገኝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ሲሆን በሳይካትሪና በፍልስፍና መስኮች ሁለተኛ ዲግሪውን ሰርቷል፡፡ በልቦለዱ አለም *ቤት የማይመቱ ሃሳቦች* የሚል የግጥም መድብል አለው፡፡

የመጽሀፉ ህትመት ዘመን - 2009 ዓ.ም.

የገጽ ብዛት - 373

የልለቦለዱ ዘውግ - ረጅም ልቦለድ

የልቦለዱ ገጸባህሪያት - ዋና ዋና ገጸባህሪያት ደስታ፣ ክብሩ፣ ውቢት፣ ሰብለ ናቸው

ልቦዱን ለመረዳት የተለያዩ ንድፈሃሳቦች/ቲዎሪዎች/ ግንዛቤ ውስጥ ገብተዋል፡፡ የነገረ ህላዌ፣ የስነልቡና፣ የስነተረክ ንድፈሃሳቦችን እንደአስፈለላጊነቱ በመጠቀም (Eclectical reading) ንባብ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

## አጽመ ታሪክ

ዶ/ር ደስታ፣ ዶ/ር ክብሩ እና ውቢት አንድ ሆስፒታል ውስጥ የሚሰሩ የህክምና ባለሙያዎችና መምህራን ናቸው፡፡ ጓደኞችም ናቸው፡፡ ክብሩ ወግ አጥባቂ አይነት ነው፡፡ ደስታ ቀለል ያለ መጠየቅ፣ በተለየ መንገድ መተርጎምና የተለመደውን ማፍረስ የሚወድ፣ ያመነበትን ፊት ለፊት የሚናገር የፈላስፋነት ባህሪ የሚታይበት ሰው ነው፡፡ ዶ/ር ውቢት የዶ/ር ክብሩ የቅርብ የሥራ ባልደረባ ስትሆን ከደስታ ጋር ከተዋወቀች ወዲህ በባህሪ መግባባት ብቻ ሳይሆን ደቀመዝሙሩም ሆናለች፡፡ መጠየቅ ነገሮችን ለየት ባለ መንገድ መረዳት ጀምራለች፡፡ ክብሩና ውቢት ቢፈላለጉም ደፍረው ፍቅራቸውን መግለጽ አልቻሉም፡፡ ደስታ በመኪና ግጭት ምክንያት አደጋ ደርሶበትና የሰው ህይወት ጠፍቶ ስለነበር ክስ ተመስርቶበታል፡፡ ውቢት ሰብለ፣ አይዳና ዊንታ የተባሉ ጓደኖች አሏት፤

[1]ባሕር ዩኒቨርሲቲ

ሰብለ ጠበቃ ስለነበረች ደስታ ጥብቅና እንድትቆምለት በመፈለጉ ይቀራረቡና ግንኙነታቸው ወደፍቅር ይለወጣል፡፡ ውቢትና ክብሩም ፍቅራቸው አጋጣሚ ተፈጥሮለት ይፋ ይወጣና ትጸንሳለች፡፡ ሆኖም ክብሩ የመጸነሷን የምስራች ሲሰማ ባሳየው ሁኔታ ውቢት ይከፋትና ይቀያየማሉ፡፡ ደስታ ጠበቃ እንደማያስፈልገውና ለራሱ ጉዳዩን መከታተል እንደሚችል ሰብለን አሳምኗት ሲከራከር ይቆይና በገዛ ወንድሙ ዳኝነት 15 ዓመት ተፈርዶበት ማረሚያ ቤት ይገባል፡፡ ሰብለ ትጸንሳለች፤ የነገራትን አምና ጥብቅና ልትቆምለት ባለመቻሏ ትጸጸታለች፤ ደስታ ማረሚያ ቤቱን ከብዙ የመኖር ጣጣዎች ነጻ ያደርገኛል ብሎ ቢያስብም ከግጭቱ ወዲህ ይሰማው የነበረው ራስ ህመም እየጠነከረ መጥቶ ሆስፒታል ይገባል፡፡ በሚሰራበት ሆስፒታል አፋጣኝ ህክምና ማግኘት ባለመቻሉ ሲንገላታ ይቆይና የመተንፈሻ መሳሪያ ተገጥሞለት ለሳምንታት ራሱን ስቶ ይቆያል፡፡ ክብሩ ደስታ አለመትረፉን ሲረዳ መተንፈሻ መሳሪያውን ይነቅለውና ይሞታል፡፡ ክብሩ በሰራው ወንጀል ይታሰራል፡፡

## ስለልቦለዱ አይነትና ስለዝርያው ንድፈሃሳባዊ መግለጫ

### ስለ ልቦለዱ አይነት

*አለመኖር* በይነአሃዳዊ ንባብ የሚፈልግ በይነዲሲፒሊናዊ ልቦለድ ነው፡፡ በሌላ በኩል የሥነጽሑፍ፣ የነገረ ህላዌ፣ የስነልቡናና የሚት ፍልስፍናዎች ተራክቦ የሚያደርጉበት ልቦለድ በመሆኑ በይነዲሲፒሊናዊ ነው ማለት እንችላለን፡፡ የዚህ ትችት ርእሱ ‹‹በይነዲሲፒሊናዊ ንባብ በ*አለመኖር*›› የተባለበትም ምክንያት ይህ ነው፡፡

*አለመኖር* የነገረ ህላዌ ልቦለድ ነው፡፡ ልቦለዶች ነገረ ህላዌ ልቦለዶች ናቸው የሚባሉት በሶስት ምክንያቶች ነው፡፡ የነገረ ህላዌ ፍልስፍና እንዲያራምዱ ታስበው ሲጻፉ፣ ደራስያኑ የነገረ ህላዌ ፈላስፎች ሲሆኑ፣ አነሰም በዛ በድርሰቶቹ የነገረ ህላዌ ፍልስፍና መገለጫ ነጥቦች ሲንጸባረቁባቸው ነው፡፡ *አለመኖር* ነገረ ህላዌ ልቦለድ ነው ለማለት ያስደፈረኝ በድርሰቱ የነገረ ህላዌ አስተሳሰቦች ስለሚንጸባረቁበት ነው፡፡ ደራሲውም ቢሆን ፍልስፍና ተምሯልና ፍልስፍናውን በልቦለዱ እያንጸባረቀ ሊሆን ይችላል የሚል መላምት ማስቀመጥም ይቻላል፡፡

የሥነጽሑፍና ፍልስፍና ግንኙነት በተለያየ መንገድ ይገለጻል፡፡

- ሥነጽሑፍና የሥነጽሑፍ ንድፈሃሳቦች ከፍልስፍና ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ማርክሳዊ ሂስ፣ ነገረ ህላዌ ሂሰ አስረጂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

- የሥነጽሑፍ ባህሪ ያላቸውና እንደሥነጽሑፍ በፍቅር የሚነበቡ የፍልስፍናዎች ሥራዎች አሉ፡፡ በሌላ በኩል የፍልስፍና ሥራዎች በግጥም፣ በምልልስ፣ በሀተታ መልክ (ሚዲያ) ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
- ፍልስፍናዊ ልቦለዶች፣ ግጥሞች፣ ቲያትሮች አሉ፡፡
- ፈላስፎቹ ገጣምያን፣ ጸሐፊ ተውኔት ወይም ልቦለድ ጸሐፍት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በተለይም የነገረ ህላዌ ፍልስፍና አራማጆች የነበሩት Simone de Beauvoir, Gabriel Marcel, Jean-Paul Sartre እና Albert Camus የፈጠራ ጽሑፍ ጸሐፍያንም ስለነበሩ፣ የነገረ ህላዌንም ፍልስፍና ቀድመው ያስተዋወቁት በሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው ስለነበር ነገረ ህላዌ እንደሥነፅሑፍ የተወሰደበትም ሁኔታ ነበር፡፡

*አለመኖር* ሥነልቡናዊ ልቦለድም ነው፡፡ ሥነጽሁፍ ከሥነልቡና ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ ጋብቻቸው በብዙ መንገድ ይገለጻል፡፡

- ሥነልቡናው በልቦለድ ውስጥ ይገለጻል፡፡ ልቦለዱ ሥነልቡናን ይበልጥ ለመረዳት ያግዛል፡፡
- ሁለቱም ቶኪንግ ኪዩር የሚሏቸው ናቸው፡፡
- ሥነልቡናዊ ንድፈሃሳቦች ለምሳሌ Oedipus Complex, Electra Complex መሰረታቸው የተጣለው ከሥነጽሑፍ ነው፡፡
- ሥነልቡናዊ ልቦለድ፣ ሥነልቡናዊ ሂስ፣ ሥነልቡናዊ ግጭት፣ እንደወረደ (ስትሪም ኦፍ ኮንሸየስነስ)፣ ውስጣዊ ግለወግ (interior monologue) የመሳሰሉት ሥነጽሑፋዊ እሳቤዎችና ቴክኒኮች ከሥነልቡናና ሳይካትሪ ሳይንሶች የተወሰዱ ናቸው፡፡
- የሥነልቡናውም የሥነጽሑፉም ሰው የሰውን ማንነት ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
- ሥነጽሑፉ የስነልቡናው ‹‹ኪኒን›› የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ የፈጠራ ሥራ እንዲያነብ ታማሚው ሊመከር ይችላል፡፡
- ማንበብ የአዕምሮ ሴልን እንደሚያነቃቃም ይታመናል፡፡

## የድርሰቱ የይዘት ትኩረት

*አለመኖር* ከላይ እንደተገለጸው በፍልስፍና የተቀነበበ ነው፡፡ በተጨማሪ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ትችትም ነው፡፡ እነዚህን እያንዳንዳቸውን በተናጥል እንመለከታለን፡፡

ፍልስፍናን አስመልክቶ ልቦለዱ የነገረ ህላዌ ፍልስፍናና የሥነልቡናና የስረመሰረታዊ/ሚታዊ ንድፈሃሳቦች አስተሳሶቦች ይንጸባረቁበታል፡፡ ፍልስፍናዎቹ በገጸባህሪያቱና በተራኪው አንደበት ይነገራሉ፤ በተግባራቸው በታሪኩ ሂደት ይገለጻሉ፡፡

ነገረ ህላዌ ኑረትን/ህልውናን የሚያጠና ፍልስፍና ነው፡፡ ትኩረቱን ኑረትና ህልውና ላይ አድርጎ የተነሳ የፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡ መሰረቱን የጣሉት እነ አርስጣጣሊስ ይሁን እንጂ በ19ኛው ክፍለዘመን እነ Soren Kierkegaard እና Friedrich Nietzsche በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተለይም ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች ተከትሎ እነ Martin Heidegger በተለይም Jean-Paul Sartre እንዳስፋፉት ይታወቃል፡፡ ነገረ ህላዌ አንድ ወጥ መልክ የሌለው ፍልስፍና ይሁን እንጂ ሴክቶቹ ህልውና/ኑረት ላይ ማተኮራቸው አንድ ያደርጋቸዋል፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ ፒሬ ማኳሪን ጠቅሶ እንደሚገልጸው በብዙዎቹ ህልውናዊ ፈላስፎች ሥራዎች ውስጥ ተመላልሰው የሚመጡ ጭብጦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ወገን ለአንድ ሰው ግለሰባዊ ማንነት መሰረት የሆኑ ጨመቅና ህልውና(essence and existence)፣ ምርጫና ውሳኔ (choice and decision) ነጻነትና ኃላፊነት (freedom and responsibility) ናቸው፡፡ ወንጀለኝነት፣ ባይተዋርነት፣ ቀቢጸ ተስፋ ሞት ሁለተኛው ወገን ሲሆኑ፣ ሶስተኛው ወገን ደግሞ የሰው ልጅ የስሜት ጣጣ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ስጋት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ጭብጦቹ አንዱ ከሌላው ተነጥለው የሚከሰቱ አይደሉም፡፡ (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ገጽ 143)፡፡

በአለመኖርም ደስታ በየአጋጣሚው ሲያነሳቸውና ሲጠይቃቸው የነበሩና በነደስታ ህይወት የተንጸባረቁት ጉዳዮች ከፊሎቹ ከነዚህ ህልውና/ኑረት፣ ስጋት፣ ነጻነት ከመሳሰሉት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

ለነገረ ህላዌ መስፋፋት በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት ሰዎች ዋነኛው ሳርተር (Sartre) ነው ብለናል፡፡ ሳርተር በጦርነቶቹ ምክንያት ተሰቃይቷል፡፡ ቤተሰቡን አጥቷል፡፡ አባቱን ያጣው በሁለት አመቱ ነው፡፡ ያደገው በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ በናዚዎች እስር ቤት ወስጥ ታስሯል፡፡ በገዥዎቹ የተጫነበትን ህግ እንዲያከብርና እንዲከተል ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ (Albert Camus ሆነ Maurice Merleau-Ponty (1908—61) በሁለተኛው አለም ጦርነት አባታቸውን አጥተው በድህነት ተጎሳቁለው ያደጉ ናቸው)፡፡ በዚህም የተነሳ ህይወትን መራር አድርጎ ነው ያያት፣ ፈጣሪን ይጠራጠራል፣ ይክዳል፡፡ ፈጣሪ ከሌለ ሰው ሆኖ መገኘት በራሱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ሰውነት ቀዳሚ ነው፡፡ ከዛ በኋላ ነው ኤሰንስ (ለህይወት ግብ ማበጀት የምትችለው) የሚያስፈልገው፡፡ ሀኪም መሆን፣ መሀንዲስ መሆን. የምትችለው.)፤ እነዚህን ሆኖ ለመገኘት

ነጻነት ያስፈልጋል፡፡ በነጻነት ያሰቡበት ለመድረስ ጥረትና ሃላፊነትን ማወቅ ይገባል፡፡ ከዛ ውጭ ይህች አለም የስጋት ናት፡፡

ይህ ፍልስፍና አንድም በቅውድ መግለጫው፣ አንድም በገጸባህሪያቱ ንግግር አንድም በግብራቸው ይገለጻል፡፡ ለምሳሌ በቅውድ መግለጫው የልቦለዱ ርእስ ‹‹*አለመኖር* ›› ሆኖ ንኡስ ርእሱ ‹‹የምንኖረው አለመኖርን በመስጋት ነው›› የሚል ነው፡፡ አለመኖር/ሞት የነገረ ህላዌ (existentialism) ፍልስፍና ማጠንጠኛ ሃሳብ ነው፡፡ መኖርም ቢሆን ደስታ እንደሚለው ‹‹እስር ቤት ነው›› በተለይ ጥረትና ትክክለኛ ምርጫና ውሳኔ ካልተደረገበት፡፡ (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 316)፡፡ ተጨማሪ ማስረጃዎች እንመልከት፡-

- ✓ ‹‹በእናታችን ማህጸን ሁሉም ነገር አለ፤ የምናውቀው መኖርን ብቻ ነው፤ መወለድ ግን አለመኖርን አመላካች ነው፡፡ ይህ ስጋት በህይወታችን ሙሉ የሚዘልቅ ነው፡፡›› (ስጋት የህልውናውያን አብይ ጭብጥ ነው፤ጥቅሱ ደስታ በምዕራፍ አንድ የሚናገረው ነው)
- ✓ ‹‹መወለድ ምንድን ነው? ለመሞት መኖር… የሞት ሂደት የመጀመሪያ ቀን›› (ደስታ እንደሚለው) (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 92) ሞት የነገረ ህላዌ ዋነኛው የፍልስፍና ጉዳይ ነው፡፡
- ✓ ‹‹ዋናው ነገር መኖር ነው፤ ይኸው እኔም አንተም አንድ መናኛ ስፍራ እንተኛለን›› (ደስታ ታስሮ በነበረበት ሰዓት አንድ በሌብነት ዘወትር የሚታሰር ታራሚ የተናገረው ነው፡ ፡) ይህ የነገረህላዌን ‹‹ Existence precedes essence>> መርህ ገላጭ ነው፤
- ✓ እንዲሁም በምእራፍ 14 ደስታ ያክማቸው የነበሩ አዛውንት ከሶስቱ የደስታ ህክምና ተማሪዎች ጋር አያይዘው ‹‹የድሮ ተማሪ አይዋደድም ነበር፣ አንዱ በአንዱ ላይ ሸር መስራት መተነኳኮል ነበር፡፡ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም የድሮ ሰው አብሮ መስራት እያቃተው የቀረ››. ብለው ትንሽ ይቆዝመና ‹‹ይቅር ግድ የለም ብቻ ዋናው መኖር ነው፡፡›› (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 167) ሲሉ ይደመጣሉ፡፡
- ✓ ነገረ ህላዌያውያን ኑሮን ቀላል አድርገው አያዩትም፡፡ ኑሮ ስጋት የሰፈነበት መሆኑን ነው የሚገልጹት፡፡ በልቦለዱም በምዐራፍ 24 መጨረሻ ደስታ ‹‹መኖር ከባድ ነገር ነው ካለመኖር ግን ይሻላል›› (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 268) ሲል ይደመጣል፡፡

- ✓ ‹‹ሰው መሆን ነው ትልቁ ማንነት፡፡ አንተ ጥቁርም አፍሪቃዊም.ሃኪምም ጓደኛም ክርስትያንም መሆኑ አይደለም ቁምነገሩ፡፡ ሰው መሆንህ ነው የሚቀድመው፡፡ የሚዘልቀውም…›› ይህ የደስታ ንግግር ነው፡፡ ስለሰው መሆን፣ ስለሞት፣ ስለመወለድ በተለይም በምዕራፍ 9 ደስታ ሆስፒታል ተኝቶ በነበረበት ወቅት ክብሩ ሊጠይቀው መጥቶ ሳለ ሲያወሳ ይደመጣል፡፡ በተጨማሪም ሰው ምንድን ነው? ከእንስሳ በአካባቢያችን ከምናየው ተፈጥሮ ምን ይለየዋል (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 331) ሞት ምንድን ነው?የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ይጠይቃል (ዳዊት፣ 2009፣ ገጽ 94፣111)

የገጸባህሪያቱም ማንነትና የታሪኩ አካሄድ በዚህ ፍልስፍና የተቀረጸ ይመስለኛል፡፡ ደስታ እንደፈላስፋ የሚቃጣው ነው፡፡ ደስታ እንደነሳርትር ሁሉ አባቱ የሞቱት በህጻንነቱ ነው፡፡ በ8 ዓመቱ ያውም በልደቱ ቀን ልደቱን እንዲያከብሩለት ለመጠየቅ ሲነካካቸው ራሳቸውን ስተው ኖሮ ሲወድቁና በዚሁ ህመም ራሳቸውን ስተው 2 ዓመት መሉ ተሰቃይተው ሲሞቱ አስተውሷል፡፡ ይህም የደስታን ደስታ ቀምቷል፣ ሲያደናግረውም ኖሯል፡፡ መደናገሩ ደግሞ በደስታ ጭንቅላት ተቀብሮ ኖሮ ስለህይወት እንዲጠይቅ እንዲፈላሰፍ ምክንያት ሆኖታል፡፡ ደስታ ደጋግሞ የሚመክረው ዛሬን እንድንኖርባት፣ እንድንሰራባት ነው፣ ትናንት አልነበርንም ነገም አንኖርም፡፡ደስታ ፈጣሪንም ለመቀበል እርግጠኛ አይደለም፡፡ ቤተክርስቲያን ደጃፍ በሩን ተሳልሞ ምንም ሳይጸልይ ተመልሷል፡፡

ምናልባትም ደራሲውም ዳዊትም ቢሆን ከቴለቪዥን ቃለመጠይቁ እንደተረዳሁት ከሞት ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጦ እንደነበር ይገልጻል፡፡ ይህ ገጠመኙ ከፍልስፍና ዕውቀቱ ጋር ተያይዞ *አለመኖርን* በነገረ ህላዌ ፍልስፍና እንዲጽፈው ምክንያት ሆኖታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በነገረ ህላዊ ቋንቋ ሰው ሃላፊነት ተሰምቶት በመረጠው መንገድ መትጋት እንደሚገባው ስለተረዳ ዘላለማዊ አድርጎ የሚያኖረው ስራውን ለህትመት አበቃ ማለት ይቻላል፡፡

ደስታ ሃኪም ለመሆን የፈለገበት ምክንያት ምናልባትም አባቱ በህመም ሲሰቃዩ በልጅነቱ ማስተዋሉ ነው፡፡ ይህ ከስነልለቡና አንጻርም ከነገረ ህላዌም አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡ ከነገረ ህላዌ አንጻር ለህይወት ምርጫና ግብ እያስቀመጠ ነው፡፡ Essence ያልነው መሆኑ ነው፡፡ ይህን አውን ለማድረግ ሃላፊነት በተመላበት መንገድ መትጋት ይገባዋል፡፡ ደስታ በማስተማር ስራውም ሆነ በህክምናው ዘርፍ የተከበረበትም ምክንያት ይህ ነው፡፡

የደስታ በመኪና የሰው ህይወት አጥፍቶ ለተከሰሰበት ክስ ጠበቃ አለማቆሙና መታሰሩ (ጠበቃዋም ፍቅረኛው ስለሆነች ዳኛውም ወንድሙ ስለሆነ አድሎ እንዲያደርጉ አልፈለገም) በዚህም ምክንያት በራሱ ጉዳዩን ሊከታተል መወሰኑና (ይህም ምርጫ ነው) 15 ዓመት እስራት ተፈርዶበት አፋጣኝ ህክምና አጥቶ በህመም መሞቱ፣ የሴቶቹ የሚወዱትን ጥንዳቸውን ማጣት፣ የክብሩ ብቸኝነት የነገረ ህላዌ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ባይተዋርነት፣ ስጋት፣ ሞት የነገረ ህልውና ጭብጦች ናቸው፡፡ ሰብለ ያለአባት ልጅ ልታሳድግ ነው፡፡ ለነገሩ ደስታም፣ ክብሩም ሰብለም፣ መኮንንም ቢሆኑ ዘግይተው ትዳር የፈለጉ ጎልማሶች ናቸው፡፡ በባይተዋርነት ከርመዋል፡፡

በገጽ 296 ስለልዩነት ደስታ ሲያወራ ‹‹ወንድ ወይም ሴት መሆን ባጋጣሚ እንጂ በምርጫ የመጣ አይደለም፡፡ የትውልድ ቦታም አጋጣሚ ነው፡፡ እናትና አባትም በአጋጣሚ ነው እንጂ በምርጫ አይደለም፤ በመሆኑም እነዚህ ያጋጣሚ ክስተቶች ማንነታችንን ብዙም ሊወስኑት አይገባም ነበር›› ይላል፡፡ ነገረ ህልውናውያን በአጋጣሚ ነው የሚያምኑት፡፡ ፈጣሪ የለም፡፡

በሥነልቡናም ረገድ የሚከተሉት አስረጂዎች ናቸው፡፡ የክብሩ ውቢትን ማፍቀሩን መግለጽ አለመቻልና መጸነሷን ለመቀበል መቸገር የመነጨው ከባህሪው አስቸጋሪነት አልነበረም፡፡ ምክንያቱ የቀድሞ ፍቅረኛው መአዛ በእርግዝና መሞት ነው፡፡ ያፈቀራት ሴት ጸንሳ እንደመዓዛ ብትሞትብኝስ ከሚል ስጋት ነው፡፡ ‹‹ዲፌንስ መካኒዝም›› ነው፡፡ ስለጠላት ሳይሆን ስለሳሳላት ነው፡፡ ይህ በገሃድ በልቦለዱ በደስታ አማካኝነት የተገለጸ ነው፡ ፡

‹‹ሰው የሆነውን የሚሆነው በአጋጣሚ አይደለም፤ አዋቂው ሰው ህጻኑ ልጅ በልጅ አዕምሮው የጻፈውን ተውኔት የሚተውን ተዋናይ ነው›› (ዳዊት፣ 2009፣ ገጽ 63) የሚለው ሥነልቡናዊ አባባልም በክብሩ፣ በደስታም ሆነ በአይዳ ህይወት ውስጥ ማስተዋል የሚቻል ነው፡፡ ለክብሩ መቆለል፣ ክብር መፈለግ፣ አንደኛ ነኝ ባይነትና ሽንፈትን ያለመቀበል ባህሪ ምንጩ አባቱ ናቸው፡፡ የመጀመሪያም የመጨረሻም ልጅ በመሆኑ አባቱ ያሳዩት የነበረ ፍቅርና ከሳቸው የነበረው ቁርኝት እና የሚያይበናቸው የሞገደኝነት ባህ ነበር የመቆለል ባህሪ እንዲይዝ ያደረገው፡፡ አባቱ ‹‹በክርታስ ተሸፍኖ ነው የተወለደው›› ይሉ ነበር፡፡ ክብሩ በልጅነቱ ከልጅ ተጣልቶ በመሸነፉ ፈረ! ፈሪ! እያሉ የተሳለቁበትና ደበደቡኝ በማለቱ የደረሰበት ተግሳጽ ሁሉ መደፈርን እንዲጠላ አድርጎታል፡፡ እሱም ቢሆን ሁለተኛ ላለመሸነፍና ሁሌ አንደኛ ለመሆን ለራሱ በወቅቱ ቃል ገብቶ ነበር፡፡

የደስታ ጠያቂነትም በአባቱ ድንገተኛ ህመምና ሞት ምክንያት በተፈጠረው ጭንቀትና ግራ መገባት የተፈጠረ ነው፡፡ በራሱ ውስጥ ለመደበቅ፣ ነገሮችን ለመርሳት በሚያደርገው ጥረት፡፡ የጠፈጠረ ነው፡፡ የደስታ ሃኪም የመሆን ሃሳብ የተጠነሰሰውም የአባቱ ህመምና ሞት ከፈጠረበት መደናገር ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በሥራውም ታታሪ መሆኑ የአባቱን ሞት በማሳብ ሌሎችን ለመርዳት ካደረበት ስሜት ነው፡፡ (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 94)

አይዳ አባቷ ወታደራዊ መኮንን ስለነበሩ፣ ያሳደጓት ከወታደራዊ ስርዓት ባልተናነሰ መልኩ ነው፡፡ እንደልቧ ከቤተሰቡ ተጫውታ አላደገችም፣ የምታያቸው እንኳን በሳምንት ነው፡፡ እንደልጅ ተጫውታም አላደገችም፡፡ ተግባሯ የታዘዘቸውን መፈጸም ብቻ ነበር፡፡ በሶስትና አራት አመቷ ልጆች ያላቸውን ነጻነት እንኳን አላየችም፡፡ መቃወም አትችልም፡፡ ትቀምሳለች፡፡ ስለዚህ ዛሬ አይዳ ዝምተኛ ብቻ ሳትሆን ታዛዥም ነች፡፡ ከአቻዎቿ እንኩዋን ፈተት ብላ ስትጫወት አትስተዋልም፡፡ ሥለዚህ ለአሁኑ ባህሪያቸው በልጅነት ያለፉበት ልምድ መሰረት ጥሏል ማለት ይቻላል፡፡ ልጁ የሰውየው አባት ነው የሚባለው ሥነልቡናዊ አባባል ነው በድርሰቱ የታየው፡፡

ስረመሰረታዊ/ሚታዊ ፍልስፍናና አስተሳሰብን አስመልክቶ ደግሞ የሚከተሉትን አስረጂዎች እንመልክት፡-

ሚት (myth) ከሰው ልጅ ህልውና ጋር ተቆራኝቶ አስተሳሰቡን አነጋገሩን እና ድርጊቱን ጭምር እየቀረጸ ዛሬን የዘለቀ ሁለንተናዊ ክስተት ነው፡፡ … እያንዳንዱ ዘመን የእኔ የሚለው ሚት አለው፤ ነገር ግን የትኛውም ሚት ባዶ ነገር ላይ አይገነባም፤ ነባሩ የሚት ልማድ የአዲሱ የሚት ልማድ ወላጅ ነው (ቴዎድሮስ፣ 2001፣.ገጽ 102)፡፡ ከገጸባህሪያቱ ንግግር ለዚህ አስተሳሰብ ማሳያ መንቀስ ይቻላል፡-

- ‹‹አንተ ሁሉም ነገር የሚገርምህ ሰው ነህ፡፡ እኔ ደግሞ ሁሉም ነገር የተደገመ እንጂ አዲስ አይደለም የምል ነኝ›› (ውቢትም ሆነ መዓዛ ለደስታ ሚስጥራቸውን ይነግሩት ስለነበር ክብሩ የአንተ ሰብለ ለኔ ለምን አትነግረኝም ብሎ ሲጠይቀው የሁለቱን ባህሪ አነጻጽሮ የተናገረው ነው (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 265)
- **ሁላችንም የትላንት ታሪክ ባሪያዎች ነን** (ክብሩ ለውቢት ስለቀድሞ ፍቅረኛው መዓዛ ለምን አልነገርካትም የሚል ጥያቄ አንስቶበት ምን ብየ ነው የምነግራት ብሎ ሲመልስለት የተናገረው ነው (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 265)
- ውቢትና ክብሩ ፍቅር ከጀመሩ በኋላ የምስራች ልትነግረው ቢሮው በገባችበት ወቅት የትምህርት ዕድል አግኝታ ነው ብሎ

በመገመት ‹‹ትምህርት ተፈቀደልሽ›› ብሎ ሲጠይቃት ‹‹በቃ ከዚህ ውጭ የምስራች የለም አይደል ለአንተ›› ብላ ስትለው ‹‹ሌላ ምን አለ ብለሽ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ያልሆነ ወደፊት የሚሆን ምንም አዲስ ነገር የለም›› ይላታል፡፡ ይህም የስረመሰረታውያን እሳቤ ነው፡፡

- ✓ ‹‹የሰው ልጅን ጥንተ ታሪክ ብትመረምር የምታገኘው ይህንኑ ነው፤ ህመም ሁሌም ከሰው ጋር አብሮ የነበረ ነው፡፡ ህክምናም እንዲሁ፡፡ አሁን ያሉን መድሃኒቶች ያልተፈጠሩበት ዘመናትም ቢሆን ሰዎች ታክመው ይድኑ ነበር- በታሪክ ሂደት የተለወጠው የመድሃኒቱ አይነት እንጂ የአካሚው ማንነት አይደለም፡ አካሚው ድሮም አሁንም ያው ነው፤ ያ የተከበረ አዋቂ ደግ ርህሩህና ለሰው ደራሽ የሆነ ሃኪም ነው፡፡ ድሮ ሰዎች በዕውቀቱ መርጠው ይሾሙታል፡፡ አሁን ደግሞ ትምህርት ቤት አስገብተው አስምተምረው ይመርቁታል፡፡ ዞሮ ዞሮ በሁለቱም ዘመን የነበሩ ሰዎች ሃኪሙ ከህመማችን ይፈውሰናል ብለው ያምናሉ፡፡›› (የክብሩ ጓደኛ ወደ ግል ስራው ለመሄድ ሲያስብ ትንሽ ተጫውተህ አትሄድም ባለው ሰዓት ክብሩ በሽተኞቼ ይጠብቁኛል ሲለው ሃኪም የሚያድነው ተጠብቆ ሲመጣ ነው ከሚለው ጋር ተያይዞ የተናገረው ነው (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 36)፡፡

ሥርዓተ ጾታንም አስመልክቶ በልቦለዱ ምእራፍ 26 የውቢትን ምስራች ለመስማት ሉሲ ከተገናኙበት ቅጽበት ጀምሮ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ሰዓት ደርሶ ሂሳብ እንዲከፍሉ በተጠየቁበት ሰዓት ሰብለ በይ የምስራቹን ንገሪን ባለችበት ሰዓት ደስታ ምን ያደርግልኛል የተደሰትሽው አንቺ እኔ ባውቀውስ ባላውቀውስ ምን ይጨንቀኛል›› ብሎ ሲናገር ክብሩ‹፣እውነቱን ነው ዋናው አንቺ መደሰትሽ ነው›› ይላል ፡፡ ሆኖም ሰብለ ‹‹ብሎ ነገር የለም እንስማውና ከዚያ የደስደሱን እንዝናናለን›› በማለቷ ክብሩ ‹‹አይ የሴት ነገር›› ይላል፡፡ ይህን ተከትሎ የሴትነት ጉዳይ በየምእራፉ መነጋገሪያ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በገጽ 294-295 ደስታ በውቢት፣ሰብለና ክብሩ መካከል የተፈጠረውን በማስታወስ ‹‹አለም የወንዶች ናት፡፡ የወንዶች ሆና ግን አልተፈጠረችም፡፤ ወንዶች ባል ሆነው ሚስትን ይገዛሉ፡፡ አባት ሆነው ልጆችን ይገዛሉ፡፡ መሪ ሆነው ሀገርና ይገዛሉ፡፡ እንዲህ እንዲፈነጩ የፈቀደላቸው ማነው? ሴቶችንስ ለመጨቆንና ለመገዛት ላለመከዳትና ለመጣል የዳረጋቸው ምንድን ነው? ›› ሲል ይደመጣል፡፡

*አለመኖር* ማህበራዊ ትችትም ነው፡፡ በየአጋጣሚው ደስታም፣ ተራኪውም ይተቻሉ፡፡ ማህበረሰቡን፣ ግለሰብን፣ ሃኪሙን ተማሪውን፣ መንግስትን ራስ ወዳድነትን፣ ፍርሃትን ይተቻሉ፡፡ ለምሳሌ

ማስመሰል ጋር በተያያዘ ደስታ እንዲህ ሲል ይደመጣል፡-

- ✓ ‹‹አሁን ዘመን ከማስመሰል በዘለለ ነገርን የመረዳት ወይም የማወቅ ፍላጎት ደግሞ ጠፍቷል፡፡››

በተጨማሪም ክፍል ውስጥ ከተማሪው ጋር በሚያደርገው መስተጋብር ደስታ እንዲህ ሲል ተደምጧል

- ✓ ‹‹ የፈራኸው ለራስህ ነው ፤ ራስህ ላይ መጥፎ እንዲደርስብህ ስለማትፈልግ፣ በዚህ ምክንያት ነገሮች ትክክል መሆን አለመሆናቸው ሳይሆን የፍትህ መሟላት ወይም መጓደል ሳይሆን አንተላይ የሚደርሰው ነገር ክፉ ወይም በጎ መሆኑ ማድረግ የምትችለው ብዙ ቢሆንም ማድረግ አለማድረግህን ይወስነዋል፡፡ ያ ደግሞ አኗኗርህን ይወስናል፡፡ ወይ ታስመስላለህ አሊያም አታስመስልም፡፡ ካስመሰልክ ከሰው ጋር በሰላም ትኖራለህ እቢኝ ካልክ ደግሞ ትገለላለህ፤ በቤትህ በጎረቤትህ በመስሪያ ቤትህ በሃገርህ ባእድ ትሆናለህ፡፡ … ይህ ማለት ግን በሰላም ትኖራለህ ማለት አይደለም፡፡ በማስመሰል ከሌሎች ጋ ብትኖርም ለራስህ ግን ባዕድ ነህ፡፡ ከሰው መኃል ሆነህ ከራስህ ግን ተገልለሃል፡፡ እያንዳዱ ድርጊትህ ከራስህ ወይ ከሌላው ይለይሃል፤ ትልቅ የመኖር አጣብቂኝም ይሄ ነው፡፡(ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 5)

ከትምህርት ጋርም በተያያዘ ተራኪው የሚከለውን ይናገራል፡- ‹‹የአሁኑ ዘመን ተማሪዎች የግል መብታቸውን ለማስከበር በተቻላቸው መጠን ከመጣር ወደኋላ አይሉም፡፡ ደግነቱ ብዙው ጥያቄያቸው ከምግብ መበላሸት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ለማስተናገድ ይመቻል፡፡ የተማሪዎች ንቅናቄ ከመሬት ለአራሹና የትምህርት ነጻነት ጥያቄዎች ተነስቶ በየምግብ ቤትና መኝታ ክፍሎች የአለመመቸት ጥያቄዎች አቋርጦ አሁን አሁን በብሄርና በዘር እንዲሁም የምግብ ሰዓትን ለትምህርት መሰዋት በጭራሽ የማይታለም ነው››፡፡ (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 127)፡፡

በተጨማሪም በምዕራፍ 14 በገጽ 146 ተራኪው ተማሪዎቹ ደስታን ክፍ ገብተው ሳይሆን ከክፍል ውጭ እየጠበቁት ሲያይ የገለጻቸው ‹‹ ተማሪዎቹ የመምህራኑን አለመምጣት በጉጉት ነው የሚጠብቁት፡፡ ሁልጊዜም ተስፋ አይቆርጡም፡፡ ወደክፈል መምጣት አለመፈጋቸውን ከማርፈድ ጀምሮ ክፍል ውስጥ ገብቶ ኋላ እስከመቀመጥ ከዚያም በተጨማሪ ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ከክፍል እና ከሀገር ውጭ ከሚገኙ ወዳጆቻቸው ጋር በስልኮቻቸው አማካኝነት በመገናኘት ይገልጣሉ›› ሲል ነው የገለጣቸው፡፡ ክብሩም ቢሆን ‹‹ከመግቢያው በር በቅርበት የሚገኙትን መቀመጫዎች አጨናንቀው የተቀመጡትን ተማሪዎች


ሲመለከት ‹፣ሳትመጡ ለመመለስ እንደፈለጋችሁ ያስታውቃል›› ነበር ያላቸው፡፡ ነገሩን በማጠንከርም ‹‹ ሶስት ህመም እያጠቃችሁ ነው፤ ደንታቢስነት፣ አርቆ አለማሰብና ድንበርየለሽ ራስ ወዳድነት›› ሲላቸው ይደመጣል፡፡

ፖለቲካን አስመልክቶ ደስታ ‹‹ሰው ፈዟል፣ አይጠይቅም፡፡ ሀገር እያደገ ነው ሲባል ጥሩ ነው ይላል፡፡ የሀገርና የሱ ዕድገት ተያያዥነት ይኑራቸው አይኑራቸው የሚያውቀው ነገር የለም፤ ግፋ ቢል ሀገር ካደገች እኔ ታዲያ ለምን ይርበኛል ሲል ነው የሚጠይቀው፤ እሱም ዕድገቱ ያመጣው ነው ሲባል አ..ሃ›› ብሎ ራሱን ይነቀንቃል (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 100)

## የልቦለዱ ስልት/ቴክኒክ

ልቦለዱ ትኩረቱ ይዘቱ ላይ ነው፡፡ ደራሲው በመግቢያው እንደሚለውም የልቦለዱ አላማ ‹‹የተለመደና እውነት የሚመስለውን ሁሉ በመጠየቅ ማፍረስ ነው›› ፡፡ የተለመዱ ሃሳቦችን መሞገት እንዲያስችለው የተለመደውን የልቦለድ አጻጻፍ ዘዬን አልተከተለም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በመጨነቅ ሃሳቡን እንዳያበላሸው በመስጋት ያደረኩት ስለሆነ የሚል ነው፡፡ የልቦድን አጻጻፍ ዘዬን አልተከተልኩም ማለት ግን በአጻጻፍ ዘዬ ወይም ቅርጽ ላይ አብዮት አካሂጃሁ ማለት አይመስለኝም፡፡

**የተረኩ የጊዜ አጠቃቀም**



1 2. 3. 4 5 6 7 8 9 10 11 12 13 14 15 1617 18 19 … 32 33 34 35 36 43 44

በምስሉ እንደምናየው ልቦለዱ 44 ምእረፎች አሉት፡፡ በምእራፍ አንድ ታሪኩ የሚጀምረው ዶ/ር ደስታ ክፍል ገብቶ ሲያስተምር ነው፡፡ ከክፍል ወጥተው ከዶ/ር ክብሩ ጋር ለምሳ ይወጣሉ፡፡ ምዕራፍ ሁለት ዶ/ር ደስታ ሆስፒታል ተኝቶ ነው፡፡ ለምን ሆስፒታል እንደተኛ ግን አናውቀውም፤ ተዘሏል፡፡ ይህን የምናውቀው በምዕራፍ 13 እና 14 ነው፡ ፡ እዛ ላይ በምልሰት ነው የሚነገረን፡፡ ምልሰቱ ውስጣዊ (በታሪኩ ውስጥ ነው)፡፡ በተጨማሪ ምእራፍ 2 ላይ የደስታ ሆስፒታል በህክምና ላይ መሆኑን ይነገረንና ከ3 — 8 ታሪኩ በነውቢትና ክብሩ ዙሪያ ወዲያ

ወዲህ ሲል ቆይቶ ተመልሶ ሆስፒታል ደስታ ጋ የሚመለስ በምዕራፍ 9 ነው፡፡

በምስሉ ወደኋላ (ወይም ግራ) የሚያመለክቱት ቀስቶቹ በሙሉ **በምልሰ**ት የተነገሩ ምእራፎችንና የታሪክ ገጽታዎችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ምዕራፍ 4 ዶ/ር ክብሩ በግል ወደሚሰራበት ክሊኒክ ሲሄድ ከማርፈዱ ጋር ተያይዞ አንድ ጓደኛው ያለውን በማስታዋስ የተገለጸ ትእይነት አለ፡፡ **ምልሰቱ ውጫዊ** ነው፡፡ ታሪኩ ከመጀመሩ በፊት የሆነ ነው፡፡ ምእራፍ 8 ዶ/ር ደስታና ዶ/ር ውቢት የተዋወቁበትን አጋጣሚ፣ ምዕራፍ 9 የደስታን አስተዳደግ፣ ምእራፍ 16 ደስታ ንጋት ላይ ቤቱ በረንዳ ቁጭ ብሎ ስለደስታ የቀድሞ ትዝታውን ሲያወጣ ሲያወርድ፣ ምዕራፍ 32 እና 33 ስለክብሩ የቀድሞ ፍቅረኛ ትውውቅና ህልፈት በምልሰት የሚነግሩን ናቸው፡፡ ምልሰቶቹ በአብዛኛው ውጫዊ (ታሪኩ ከመጀመሩ በፊት የተፈጸሙ) ናቸው፤ የተነገሩት ለታረኩ. ለገጸባህሪያቱ ካላቸው ፋይዳ አንጻር ነው፡፡

በሌላ በኩል ወደቀኝ የሚያመለክቱት ቀስቶች ወደፊት የሚሆነውን ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ ንግር መሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ምዕራፍ 8 ላይ ክብሩ በጥዋት በረንዳ ላይ ቁጭ ብሎ ስለአስተዳጉ ሲያስብ ቆይቶ ‹‹አይኑ አንዲት ልትፈነዳ ያለች ጽጌ ረዳ አበባ ላይ አረፈ፤፡ ከተቀመጠበት ተነስቶ አበባዋን ቀጠፋት፡፡ የቀጠፋትን አበባ ይዞ ወደ መኝታ ቤቱ በመመለስ የረገፈች ሌላ ጽጌረዳን ከአበባ ማስቀመጫው በማውጣት በአዲሷ አበባ ተካት›› (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 80)፡፡ ይህ ንግር ነው፡፡ ንግሩ የቀረበው በአበባና ማስቀመጫው ተምሳሌትነት ነው፡፡ በሚታዊ ቲዎሪ (ያንግ እና ፍሮይድ ይመስሉኛል) ጎድጓዳነት ያለው ቁስ የሴት ተምሳሌት ነው፡፡ አበባም የፍቅር ተምሳሌት ነው፡፡ የረገፈው አበባ በልቡ ውስጥ የነበረቸው የቀድሞው ፍቅረኛው መዓዛ ናት፡፡ በህይወት የለችም፡፡ አዲሱ ዕንቡጥ አበባ ደግሞ ውቢት ናት፡ በልቡ ጽፏታል፡፡ ንግሩ ውጫዊም ውስጣዊም ነው፡፡ በታሪኩ መጨረሻ አካባቢ ፍቅራቸው ይፋ ይሆንና ለጊዜው ይኳረፋሉ፡፡ በንግሩ መሰረት ምእራፍ 14 ገጽ 152 እና ምዕራፍ 34 እና 44 ላይ ከተሰጡት ፍንጮች ጋር ተያይዞ ታሪኩ ካለቀ በኋላ የውቢትና ክብሩ ፍቅራቸው ዕውን እንደሚሆን እንገምታለን፡፡

በምዕራፍ 14 ደስታ ውቢትን ‹‹ደስታ እስፔሻል›› (ሃሜት በማኪያቶ) ሊጋብዛት ፈልጎ ስልክ በደወለላት ሰዓት ረፍት ላይ መሆኗንና ስራ አለመግባቷን ስትገልጽለት ‹‹ለመሆኑ አባወራሽ አውቋል ረፍት መውጣትሽን›› ብሎ ሲጠይቃት ‹‹የምን አባ ወራ?›› ስትለው ‹‹ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ መሆኑ አይቀርም ብዬ ነው›› ሲል የሚመልስላት ውቢት ከክብሩ ጋር ሊጋቡ እንደሚችሉ ጠቋሚ ንግር ነው ማለት

እንችላለን፡፡ ተራኪውም ቢሆን በገጽ 207 ‹‹ከውቢት ጋር ያለው ግንኙነት ከቀን ወደቀን መሻሻል በማሳየቱ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ፍቅር እንደሚጀምሩ ሁለቱም በልባቸው አምነዋል፡፡ ›› ሲል ፍንጭ ሰጥቷል፡፡

በተመሳሳይ ምዕራፍ 34 እና 44 ላይ ከታሪኩ ፍጻሜ በኋላ ስለሚከሰት ጉዳይ ፍንጭ ሰጥተውናል የሚል ግምት አለኝ፡፡ የሴቶቹ መጸነስና የደስታ ለሰብለ ክብሩ ውቢት አረገዝኩ ብላ የምስራች ስትናገር የደነበረበትን ምክንያት ከመዓዛ በእርግዝና መሞት ጋር አያይዞ ውቢትም ትሞትብኛለች በሚል ምክንያት እንደሆነ መናገሩ መረጃውን ሰብለ ለውቢት ትናገርና ችግሩን ተረድታ ለክብሩ ይቅርታ አድርጋ ፍቅራቸው ይቀጥላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ እንዲያውም በገጽ 357 ደስታ ማረሚያ ቤቱ ክሊኒክ ተኝቶ ሳለ ሰብለ ማርገዟን ልትነግረው ስትፈልግ ሁኔታዋን አስተውሎ ደስታ አይኖቹ ብርሃን እየፈነጠቁ ‹‹ውበትና ክብሩ ታረቁ እንዴ?›› ሲል ይጠይቃታል፡፡ ይህ ለክብሩና ደስታ መታረቅና መጋባት ፍንጭ ሰጭ ነው፡፡

የታሪኩን ዋነኛ ጉዞ ስናየው የወራት ዕድሜ ያለው ነው፡፡ ከደስታ መገጨት እስከ ደስታ ሞት ነው የሚተርክልን፡፡ የመጀመሪያዎቹ 15 ምዕራፎች የሶስት ቀናት ታሪክ ነው፡፡ ባለበት የሚረግጥ ነው፡፡ ከደስታ አርብ ሆስፒታል መግባት እስከ እሁድ በተለየም የመጀመሪያዎን ሁለት ቀናት ትእይንቶች የሚገልጹ ናቸው፡፡ በነዚህ ምዕራፎች ጎልቶ የሚታየው በየምእራፉ በምልሰት ወደኋላ ተሂዶ የገጸባህሪያቱን አስተዳደግና ትዝታ የሚገልጽ ነው፡፡ **ምዕራፍ 20ዎቹና** ሰላሳዎቹ ስንገባ ግን ታሪኩ አላስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያስበውን ታሪክ እየዘለለ(ellipsis) ወደፊት ይገሰግሳል፡፡ የሰብለና ደስታ መፋቀርና የሰብለ መጸነስ ፣ የደስታ ችሎት መቅረብ፣ መታሰር፣ ሆስፒታል መግባትና መሞት፣ የክብሩና ውቢት ፍቅር ይፋ መሆን፣ መጋጨትና የክብሩ መታሰር፣ የመኮንንና የአይዳ የፍቅር ግኑኝነት ሁሉ የምናውቀው በቀሪዎቹ 19 ምዕራፎች ነው፡፡

ምእራፍ ሰላሳዎቹ የታሪኩ ጉዞ መፍጠን ብቻ ሳይሆን ምእራፎቹ ይቆረረጣሉ፡፡ አንድ ምዕራፍ አንድና ሁለት ገጽ ይሆናሉ፡፡ ይህ ያለምክንያት አይደለም፡፡ በዳኛቸው ወርቁ አደፍርስ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ እንደሚስተዋለው የአለመኖር ልቦለድ ገጸባህሪያት አለመረጋጋትና የስሜት መረበሽና መጨናነቅ ለማሳየት ነው፡፡ ክብሩ ከእርግዝናዋና በሴቶች ጉዳይ ከውቢትና ሰብለ መቀያየም፣ የደስታ ችሎትና የእስራት ፍርድ፣ የደስታ መታመም፣ ህክምና ማጣት፣ የሰብለና ውቢት መጸነስ በአንድም ሆነ በሌላ መለያየት አለመረጋጋትን ይፈጥራል፡፡

በልቦለዱ ዱብዕዳ የሚመስሉ ክስተቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የደስታ ወንድም መኮንን ዳኛ መሆንና የደስታን ጉዳይ/ኬዝ ማየት፤ የመኮንንና የአይዳ

ፍቅር ግንኙነት (ብዙም ፋይዳ ባይኖረውም)፡፡ የደስታ ሞትም ምክንያታዊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሃኪም ነው፡፡ የመኪና ግጭት ደርሶበታል፡፡ ራሱን እየደጋገመ ሲያመው ችግሩን መጠርጠርና ቶሎ ህክምና ማግኘት ይችል ነበር፡፡

## የልቦለዱ አተራረክ ስልት፡ መንገርና ማሳየት

ልቦለዱ በአብዛኛው በመንገር ስልት ነው የቀረበው፡፡ የተመረጠው መንገድ መንገር ነው፡፡ ምልልስ አለ፡፡ አንድን ልቦለድ ትእይንታዊ የሚያደርገው ምልልስ ቢሆንም ዕድሉ በነጻነት አልተሰጣቸውም፡፡ ሚናቸውን ይቀማል፡፡ በዚህ ምክንያት ጎልቶ የሚታየው የተራኪው ድምጽ ነው፡፡ ከዛም አልፎ ንግግራቸውን፣ ሃሳባቸውን፣ ድርጊታቸውን ሪፖረት ነው የሚያደርገው፡፡ እንዳውም ተራኪው ሁሉን አወቅ በመሆኑ በገጸባህሪያቱ ድርጊት፣ ሃሳብ ላይ አስተያየትና ዳኝነት ይሰጣል፡፡ ስለዚህ ምልልሱ ትዕይንታዊ ሊያደርገው ይችል የነበር ቢሆንም የተራኪው ጠልቃገብነትና ትችት በመጉላቱ ወደመንገር ስልት ወስዶታል፡፡

## ገጸባህሪ አሳሳል

በገጸባህሪ አሳሳል ረገድ ዋና ዋናዎቹ ደስታ፣ ክብሩ.፣ ውቢት፣ ሰብለ ሲሆኑ ሶስቱም ከህክምና ተቋም መሆናቸው ከደራሲው ልምድና ገጠመኝ የመነጨ ናቸው፡፡ ገጸባህሪያቱ እኩል ዕውቀት የላቸውም፡፡ ጠያቂው አንድ ሰው ነው፡፡ ደስታ፡፡ የደስታ መንፈስ የተጋባባት ውቢት አርአያውን ለመከተል በመፍጨርጨር ላይ ነች፡፡ ከዛ ውጭ ክብሩ የልማድ እስረኛ ነው፡፡ መዓዛም የክብሩ ጓደኛም የደስታ መንፈስ የተጋባባቸው ነው የሚመስሉት - መፈላሰፍ፣ መጠየቅ፣ የተሰማቸውን ፊት ለፊት መግለጽ፡፡

ገጸባህሪያቱ ብዙዎቹ ከአንድ ባህር መቀዳት ብቻ ሳይሆን የገደል ማሚቶ ነው የሚመስሉት፡-

- ✓ ገጸባህሪያቱ የደስታ ግልባጭ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ በእርሱ ተቀርጸዋል፡፡ ውቢት ደቀመዝሙሩ ነች፡፡ ክብሩም ቢሆን የሚላት ይህንኑ ነው፡፡
- ✓ በምእራፍ አራት ክብሩ አስታውሶት የነበር ጓደኛውም ቢሆን ያራመደው ሃሳብ የደስታን ነው የሚመስለው፡፡
- ➢ ለምሳሌ ውቢት ከክብሩ ሲከራከሩ ‹‹ ማመን የዋህነትን ይፈልጋል፣ አንተ ደግሞ በጣም ብዙ ነገሮች አሉህ የዋህ ግን አይደለህም፤ በዚህ ምክንያትም ማመን የሚለው እሳቤ ልብህ ውስጥ ሊገባም ሊቆይም አይችልም… ትለዋለች፡፡

ድፍረቷና ግልጽነቷም እንደደስታ ነው፡፡

- ✓ ለምሳሌ በምዕራፍ 4 ገጽ 29 — 30 ‹‹ክብሩን አንዳንዴ ጊዜ እኮ የምትረግጠው መሬት ያመው ይሆን? ብለህ የምትፈራ ነው የሚመስለኝ፤ ራስህን ፍታው፣ ትንሽ ለቀቅ አድርገው፡፡ ያን ጊዜ ህይወት ደስ የሚል ነገር እንዳላትም ይታይህ ይሆናል፡፡ ትለዋለች፡፡
- ✓ …ጠፍሮ ከያዘህ ወሰን የለሽ ኩራትና የአዕምሮ ጀብደኝነት፡፡ የማወቅ ጉጉትህን አብርደው ምናልባትም የምታውቀው ይበቃህ ይሆናል፡፡ ዘና በል፤ አካባቢህን እይ የምትፈልገው ነገር ሁሉ በዙሪያህ ነው፡፡
- ✓ ‹‹ሁልጊዜም ነገር ሲከር ወደቀልድ ትወስደዋለህ፡ ይህም የፈሪነትህ ሌላ ምልክት ነው፡፤ የማታሸንፍ ከመሰለህ መጋፈጥ አትልግም፡፤ የምትዋጋው እንደምታሸንፍ ርግጠኛ ስትሆን ብቻ ነው፡፡ ያ ደግሞ ጀግና አያሰኝኝም፤ ያሸነፍከው ከጅምሩ ደካማነቱን ያወቅከወን ጠላት ስለሆነ፡፡
- ✓ እኔን ከወደደድከኝ እየቀለድክ ብቻ ልትነግረኝ አትችልም የምር ማድረግ ይጠበቅብሃል፡፤ ፈሪ ስለሆንክ ግን መልሳ ባትወደኝስ ብለህ ትሰጋለህ፡፤ ይህንንም እንደ መሸነፍ ታየዋለህ፣ መሸነፍ ደግሞ ሞትህ ነው፡፡ (ዳዊት፣ 2009፣ገጽ 29 -30)( በተመሳሳይ ደስታ ክብሩን ቁልል ነህ ይለዋል፡፡)

መአዛም ቢሆን የክብሩ ደቀመዝሙር ነው የምትመስል፡፡

- ✓ ለምሳሌ ‹‹ ልጅ ትፈልጋለህ?›› እንዴ ብላ ክብሩን ስትጠይቀው ‹‹በጣም ነው የምፈልገው ሲላት ለምን ስትለው‹‹ እንደራስሽ እንደልብሽ ቀርጸሽ የምትፈጥሪው ነገር ደስ አይልም› ይላታል ‹‹ ቢሆን ደስ ይላል ግን አይሆንም›› ስትለው ‹‹ለምን›› ይላታል፡፡ ‹‹ልጅ እኮ ሌላ ሰው ማለት ነው፡፡ እንደራስህ እንደልብህ ልትቀርጸው አትችልም፤ ልጅ ቢኖርህ እንኳን እንደራሱ ወይም እንደራሷ ነው እንጂ መሆን ያለባቸው አንተ እንደፈለግክ እንዴት ይሆናል?›› ትለዋለች፡፡ (ይህን ሃሳብ በገጽ 323 ‹‹ልጅ እኮ ማለት ሌላ ሰው ማለት ነው የሚለውን ቃል በቃል በመድገም ማብራሪያ ያክልበታል፡፡ ክብሩም ‹‹ተመካክራችሁ ነበር›› ሲል ይደመጣል፡፡)

በምዕራፍ አራት ክብሩ ሃኪም ተጠብቆ ሲመጣ ነው የሚያድነው የሚለውን ትችት ሲገልጽ የክብሩ ጓደኛ ንግግሩ የደስታን ነው የሚመስለው፡፡

- ✓ ለምሳሌ በገጽ 35 ‹‹አየህ አንተ ሃገሪቱ ውስጥ በጣም አሉ ከተባሉት ሃኪሞች ውስጥ አንዱ ነህ፡፡ ልብ በል ካሉት አንዱ የተባልከው በጠም የተሻልክ የተራቀቅክ ሃኪም ስለሆንክ ሳይሆን ብዙ ሃኪም ስለሌለ ነው፡፡ ስለዚህ በታሪክ አጋጣሚ አሉ ከሚባሉት አንዱን መሆን ታድለሃል፡፡ በእርግጥ ጥቂት ሃኪሞች በመኖራቸው ምክንያት እኒሁ ጥቂቶች ያላቸው አማራጭ በጣም ጥሩ መሆን ብቻ ነው፡፡ በጥረትና በፍላጎት ምናምን ሳይሆን በግድ…. ሰው በአጠቃላይ የእኛ ሀገር ሰው ደግሞ በተለይ ለመኖር የተባለውን የሚቀበል ነው፡፡ ብዙ አይጠይቅም፡፡ አሃ! ነው እንዴ? ብሎ ነው የሚያልፈው፡፡ ያ ደግሞ በህይወት ለመቆየት አስፈላጊ ነው፡፡ አለበለዚያ መሞት ላይቀር መልፋት ለምኔ ሲል ነው፡፡ ሰው ለመኖር ሲል ስለሚፈራ ሕይወት በጣም ትርጉም ያለው ነገር ነው ሲባል ‹‹አዎ ይላል እንጂ ትርጉሙ ምንድው? ብሎ የሚጠይቅበት አጋጣሚ በጣም ውሱን ነው፡፡ ያንንም እንኳን ቢጠይቅ በቀላሉ መልስ ያገኛል፡፡ ልጅ ወልዶ ማሳደግ መስራት፣ ለሌላኛው ዓለም መዘጋጀት… ምናምን የሚሉ መልሶች ሲያገኝ ይበቃዋል፡፡ በቃ ህይወት ትርጉም አለው አበቃ›› …ስለዚህ አንተ ትድናለህ ይህን መድሃኒት ዋጠው ስትለው ያምንሃል ይድናል **እምነትህ አድኖሃል** አይደል መጽሀፉ የሚለው፡፡›› ሲል ይደመጣል፡፡ ( ይህንኑ ‹‹እምነትህ አድኖሃል›› የሚለውን አገላለጽ ደስታ በገጽ 347 ‹‹ህክምና እምነት ነው›› ሲል ይጠቀምበታል፡፡)
- ✓ በምዕራ 43 ደስታ እንደማይተርፍ ክብሩ በመገንዘቡ የመተንፈሻ መሳሪያውን ከደስታ ያወልቀውና ደስታ ይሞታል፡፡ ክብሩ የተገበረው፡፡ የደስታን ሃሳብ ነው፡፡ ‹‹ሰወች የሚሞቱ መሆናቸው ከተረጋገጠ ያለ አግባብ ህይወታቸውን ማራዘም የነሱንም ስቃይ ማብዛት፣ ሊተርፍ የሚችል ሰውንም ዕድሜ ማሳጠር የለብንም›. የሚል አቋም ነበረው፡፡

የገጸባህሪያቱ ሥም አስመልክቶ ከምግባራቸውና ከማንነታቸው ጋር የሚሄድ ነው፡፡ ደስታ ለራሱም ሆነ ለሌሎች ደስታን የሚለግስ ነው፡፡ ክብሩ ክብር ፈላጊ ነው፡፡ ውቢት ውብ ነች፡፡ ደስታ የሆስፒታሉን ደመና የገሰሰች ጸሀይ ሲል ገልጿታል፡፡

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ከላይ ባደረግነው ትንተና *አለመኖር* በፍልስፍናና በስነልለቡና ቲዎሪዎች የተዋቀረ በይነዲሲፒሊናዊ ልቦለድ ነው፡፡ ፍልስፍናው በገጸባህሪያቱ ንግግርም ግብርም ህይወትም የሚገለጽና እንደድርና ማግ

ተወሳስቦ የተሰራ ነው፡፡ ደራሲው ለቅርጹ አልተጨነቱም ይበል እንጂ ጨርሶ ከስልቱ ርቋል አፈንግጧል ማለት አይቻልም፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት


ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ *በይነዲሲፕሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፡፡

ዳዊት ወንድማገኝ፡፡ (2007)፡፡ *አለመኖር*፡ አዲስ አበባ፡፡ ደራሲው

Michelman, Sthepen (2008). *Historical Dictionary of Existentialism*. Torronto: Scarecrow Press.